# የሰላምና መረጋጋት አባት

ከብርሃኑ ተሰማ(ኢዜአ)

በሥራ ጉዳይ ጽህፈት ቤታቸው ሄጄ ያነጋገርኳቸው ሁለት የጎረቤት አገሮች ከፍተኛ ባለሥልጣናት የነገሩንን ለዘገባዩ አስቸጋሪ ሲሆንብኝ ቆይቷል።ከታላቁ የአገራችን ሰው ተነጋግረው ሲወጡ ጣል ያደረጓቸውን'' ይሄን ምን ብዬ ነው የማቀርበው?'' እያልኩ እተወዋለሁ።ሙያዊ ደረጃውን አስጠብቄና ፖሊሲዎችን አክብሬ እስከሰራሁ ድረስ አፌን ሞልቼና ደረቴን ነፍቼ በምሰራበት ሙያ ቃሉን ሳልጠቀምበት ቀርቻለሁ።

ባለሥልጣናቱ ከሱዳንና ከደቡብ ሱዳን በተለያዩ ቀናት አምና(2004) የመጡ። ተልዕኳቸው የጋራ አግባቢ ፍለጋ።ቦታው አዲስ አበባ።

ኃላፊነታቸው የሱዳኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና የደቡብ ሱዳኑ ደግሞ  የሰላም ጉዳይ ሚኒስትር።

አጀንዳዎቻቸው ሰላምን ለማምጣት በሁለቱ አገሮች መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት ለመፍታት አደራዳሪ መሻትን በዋነኝነት ይዘው ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸውን ወዳጅነት ማጠናከር በሁለተኛ ደረጃ የተያዘ ጉዳያቸው ነበር።

እንግዶቻችን በምን ጉዳዮች ላይ ተወያየችሁ ብሎ መጠየቅ የሆነው የሁለት መንግሥታዊ ድርጅቶች ጋዜጠኞች ስናነጋግራቸው የሰጡን ምላሽ ከዲፕሎማሲያዊ መሥመር ወጣ ያለ ፤የመሪያችንን ክብርና ዝና ያገነነ መስሎ ስለሚታየኝ እዘለው ነበር።ከልክ በላይ መካብ መስሎኝ።

ተወያዮቹ  ጉዳዮቹን ዲፕሎማሲው በሚፈቅደው መሠረት ይገልጹልናል።ከዚያ አልፎ ''ተመካከርን'' ቢሉ መልካም ያንን አልፎ '' መከሩን'' ወይም '' መከረውናል'' ሲሉ ''እንዴት በመገናኛ ብዙኃን ይሄ ይዘገባል?'' በማለት ሳልጽፈው የምቀር ራሴው ነበርኩኝ።ቃሉና የያዘው ሐሳብ ለእኔ በጣም ከባድ ነበር።ለዚያውም መሪም ቢሆን የግለሰብ ማንነትን አጉልቶ ለማውጣት አስቸጋሪ በሚሆንበት በእኛ ኅብረተሰብ።መሪያችን መካብና ማግዘፍ ይመስልብኛል ስል ቆይቻለሁ።ካጠፋሁ ይቅርታ።ሙያዬም  አይፈቅድልኝም ብዬ አስባለሁ።

ባለሥልጣናቱ ዛሬ አጠገባችን ከሌሉት ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጋር ያደረጉትን ቆይታ አጠናቀው ሲወጡ ጣል ያደረጓት ቃል በአንድነት ወይም በተከታታይ ገብተው የነገሩን ቢሆን እንኳን አያስደንቀኝም ነበር።በተለያዩ ቀናት ካገኘናቸው በኋላ የሰጡት ቃል የመለስን ማንነት ለማሳየት ከበቂ በላይ ለሕዝብ በዚያ መልኩ ለማቅረብ አስቸጋሪም ነበር።በተለይም ካለፉ በኋላ በተሻለ ያወቅናቸውን ሰው በዚያ ዓይነት አገላለጽ ብናቀርባቸው ቢሰሙ እንኳን የሚጣሉን ሁሉ ይመስለኛል።

ከጥቂት ዓመታት በፊት እከታተለው የነበረው ትምህርት ውስጥ ዓለም አቀፍ የፖለቲካ ጉዳዮችንን የሚመለከይ ኮርስ ተከታትያለሁ።መምህሩ የመጡት ከሕንድ ነው ወደዚህ ከመምጣታቸው በፊትም ኤርትራ ውስጥ ሰርተዋል።
ታዲያ  የአፍሪካ ቀንድ ጉዳዮች ሲነሱ የሚሉን ነገር ነበር '' አገራችሁ የምሥራቅ አፍሪካ ኃያል ናት'' ይላሉ። መሪያችንም ከፍተኛ ተሰሚነት ያላቸው የክፍለ አህጉሩ አረጋጊ መሆናቸውን ይናገራሉ።

መምህራችን የሚሉት ኃያልነት በአብዛኛው ወታደራዊ የሆነውን ዓይነት እንደሆነ እገምታለሁ። በጦር ኃይል ጉልበት በመመካት እዚህና እዚያ አለን የሚሉትን ዓይነት እንዳልሆነች የተረዱ መሆናቸውን ግን እጠራጠራለሁ።ይልቁንስ በነዚያ ዓመታት የጀመረችው የኢኮኖሚ ግስጋሴ ወደ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ እንደሚመራት ቢያስረዱን እመርጥ ነበር።

እሳቸው የፖለቲካ መምህር በመሆናቸው ዓለም አቀፋዊ የኃይል ሚዛን እንጂ፤ሌሎች ጉዳዮች እምብዛም ላይ ላይገቧቸው ይችሉ ይሆናልና አይደንቀኝም።ሆኖም የአፍሪካ ቀንድ አረጋጊ መሆናችንን አልካዱምና አንቀየማቸውም።የመከላከያ ሠራዊታችን ባህርይም ኃያልነት ሳይሆን፤ሕዝባዊነት በመሆኑ አለመረዳትም ነው።ማን መርቶት ለዚህ እንደበቃ ዛሬ ከእኛ በላይ ምስክር አያሻም።መለስ በዚህ አኩርተውናል።

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በአፍሪካ ቀንድ ሰላምን ለማምጣትና መረጋጋትን ለማስፈን ያደረጉት ጥረት ወደር እንደሌለው ይታወቃል።አገራቸውን በዚያ ጎዳና እንድትራመድ ፌዴራላዊ ሥርዓት ዘረጉ።ራሰን በራስ ማስተዳደር፣ እኩልነት፣ፍትህ፣ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደርን መተዳደሪያቸው ያደረጉ ክልሎችንም አዋቀሩ።

ከአሃዳዊ የአስተዳደር ሥርዓት ወጥተን ፌዴራላዊ ሥርዓት ለመስረት ያደረግነው ትግል በዋዛ ውጤት አላስገኘም። ጠቀሜታው ባለማወቅ ያኮረፉ ኃይሎች በየቦታው ችግር ሲፈጥሩ ቆይተዋል።ከአንዱ ክልል መሬት ሌላው መሬት ለመውሰድ የራሱን ኃይል እያደራጁ ፣ግጦሽና ውሃን እያመካኙ ችግር የሚፈጥሩም ሲያጋጥሙ ቆይተዋል።

ታዲያ ችግሮችን በትዕግሥት መፍታትና ማስታረቅን መላው ያደረገው የመለስ አመራር፣ቀስ በቀስ ግጭቶች ለአገር ዕድገትና ልማት እንዳማይበጁ ሲያስተምር፣ ሲያወያይና ሲያሳምን ቆይቷል።

አሁን አንድነቷን የጠበቀች የሕዝቦቿን መሠረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት የምትጥርና ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት እያስመዘገበች ያለች አገር ለመገንባት እየበቃች ያለችው ውስጣዊ ችግሮቿን በዚህ ዓይነት ፈትታና እየፈታችም ነው።

ለነጻነቷ ከሱዳን ጋር የተፋለመችውን የአሁኗ ደቡብ ሱዳን በሰላማዊ መንገድ እስከ ውሳኔ ሕዝብ ድረስ አብራ እንድትቆይ በማድረግ አስተዋጽኦ አድርገዋል።የደቡብ ሱዳን ሕዝብ የመገንጠል ጥያቄውን ሲያጸናውም ሁለት የተከፈለችው አገር ወደ ሌላ ግጭትና መተራመስ እንዳይገቡ በሕይወታቸው የመጨረሻ ቀናት ሁሉ ለማስታረቅ ጥረዋል።አሁንም አንዴ የሚዳፈን ሌላ ጊዜ የሚቀሰቀስ ግጭት በሁለቱ አገሮች ቢኖርም፣ተስማምቶና ተከባብሮ መኖርን ታላቁ መሪ አስተምረዋል።

ሁለቱ ሱዳኖች በመካከላቸው ችግር ከተፈጠረ መደራደሪያቸው አውሮፓ ወይም አሜሪካ አይደለም።የሁለቱ ጎረቤት፣የሁለቱም ወዳጅ፣የጋራ ቤታቸው ኢትዮጵያ ናት።የመለስ አግባቢነትና አስታራቂነት፣ፍትሃዊነትና ገለልተኝነት ስቦ ያመጣቸዋል።አንድ ውል ፈጽመው ለትግበራው ወደየአገሮቻቸው ይሰማራሉ።በመካከሉ ግጭቶች ካጋጠሙና የውሳኔዎች አፈጻጸም ጉድለቶች ካለም " ገላግሉን" ብለው ይመጣሉ።

ደቡብ ሱዳን ከሱዳን ተገንጥላ የራሷን ግዛት ስትመሰርት ድንበሮችን ለመወሰን አዳጋች ነበር።በተለይም እብዬ የተባለው ግዛት አንዳቸው "የእኔ ነው" ሲሉ ሌላኛውም "ሽረ የእኔ ነው" እያሉ እውነተኛ ባለቤቱን ለማወቅ አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል።አልፎ ተርፎም በግዛቱ ውስጥ ከታችኛው የዓባይ አገር የሚመጡ አርብቶ አደሮች ስላሉበት ችግሩ ውስብስብ በመሆን ሲያስቸግር ቆይቷል።

ሁለቱ አገሮች በሚያወዛግባቸው በዚህ ግዛት የተነሳ ሌላ ግጭትና ፍጅት እንዳይከሰት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሰላም አስከባሪ ሠራዊት እንዲያስተዳድረው ይወስናል።ለዚህ ከባድ ተልዕኮ አገሮቹን በገለልተኝነት የሚያገለግል ሰላም አስካበሪ ሠራዊት ለመመደብ ሲጠይቅ " ኢትዮጵያ" ትሁንልን ያሉት ሁለቱም አገሮች ናቸው።

እነሆ ድርጅቱ በታሪኩ ግጭቶችን ለማብረድና እንዳይቀሰቀሱ ለማድረግ ከሚያሰማራቸው የሰላም ማስከበር ተልዕኮዎች ከአንዲት አገር ሠራዊት ብቻ የተሰባሰበው ኃይል በዚያች ግዛት ይገኛል።ከዚህ በላይ መታመን ከዚህ በላይ መወደድ ከየት ይገኛል!!መለስና አመራራቸው ይህንንም አድርገዋል።

በኢትዮጵያ የደርግ አምባገነን ሥርዓት የወደቀበትን ጊዜ በሶማሊያ የዚያድ ባሬ አምባገነናዊ መንግሥት የተንኮታኮበት ጊዜ እምብዛም አይራራቁም።አስቡት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ እስካለፉበት ጊዜ ድረስ ያቺ አገር ከእርስ በርስ ግጭቶች ወጥታ አታውቅም።እንዲያውም ትናንሽ መንግሥታት ሲመሰሩባትና የጦር አበጋዞች ሲፈነጩባት ኖራለች።

መለስ ባልታከተ የሰላም ጥረትና የማረጋጋት መንፈስ የአገሪቱን አንጃዎች ለማወያየት ጥረዋል።ዛሬ የተፈረመው የሰላም ስምምነት ነገ ሲፈርስ፣ተረጋጋ በተባሉት አካባቢዎች ግጭቶች ሲባባሱ፣እልቂት ሲያጋጥም ፍጅት ሲከተል ያለመታከት ለሰላም ታግለዋል።

ሶማሊያ ዛሬ ላለችበት አንጻራዊ መረጋጋት፣ለተዘረጋው ፌዴራላዊ ሥርዓትና ቋሚ መነግሥት ምስረታም ከፍተኛ ድርሻ ካላቸው መሪዎች አንዱ መለስ መሆናቸውን የሶማሊያ መሪዎች ሲናገሩ መስማትም አዲስ አይደለም።የጎረቤት አገሮች መሪዎችና ሕዝብ፣የአፍሪካ ኅብረት፣የአውሮፓ ኅብረትና የአሜሪካ መንግሥትም ይህንኑ ሲመሰክሩ ማድመጥም ይቻላል።

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ እየፈራረሰች የነበረችውን ሶማሊያን ተገን አድርጎ በአገሪቱ ሲንቀሳቀሱ የቆዩትን የእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ኅብረት ሴራ በማምከን፣የአልቃይዳና የአል ሸባብን አክራሪዎችን በመፋለም ያደረጉት ጥረትም በታሪክ ሲወሳ ይኖራል።በቆራጥ አመመራራቸው ሽብርተኞችን ተፋልመዋል።ሌሎችንም አስተባብረዋል።አሸንፈው እንዲወጡ ሳይሆን፣ተሸንፈው እንዲወጡ በማድረግ ደማቅ ታሪክ አጽፈዋል።ለዚያውም የኤርትራ የማተራመስ ስትራቴጂ ታክሎበትና

ክፍለ አህጉሩ ከቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት ጀምሮ ከማያጣው ትርምስና መመሰቃቀል ከሚደርስበት ችግር ሙሉ በሙሉ ሳይላቀቅ።

በሩዋንዳ የተፈጸመው የእርስ በርስ ግጭት ለማስቆም ባደረጉት አስተዋጽኦ የአገሪቱን ታላቅ ሜዳሊያ ከፕሬዚዳንት ፖል ካጋሜ የተሸለሙት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሌሎች አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ሽልማቶች የሚገባቸው የጊዜያችን የሰላም አባት፣የመረጋጋት መሐንዲስ መሆናቸውን መመስከር ይቻላል።

ኢትዮጵያ  ዛሬ በዓለም አቀፍ የሰላም ማስከበር ተልዕኮዎች በአፍሪካ አንደኛ ከዓለም አራተኛ የሚያደርጋትን ኃይል በማዋጣት ግዳጇን በመወጣት ላይ የምትገኝ አገር ናት። ራሷ ያላትንና ያስከበረችውን ሰላም ሌሎች እንዲያጡት አትሻም። ሌሎች "ምን ቢያጡ ነው የተጣሉትና መግባባት ያልቻሉት?" ብላ ችግሮቻቸውን በሰላማዊ መንገድ  እንዲፈቱ አቅሟ የቻለውን ሁሉ በክፍለ አህጉራዊ፣ በአህጉራዊና በዓለም አቀፍ መድረኮች ጥረት ታደርጋለች።

ኢትዮጵያውያን ለራሳችን ያለን ግምትና ክብር  አሳንሰን የሰውን ማንነት የምናውቀው አንድም በሞት ሌላም  ተለይቶን ሲሄድ ነው ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ያለን ክብርና ፍቅር እስከወዲያኛው ከተለዩን በኋላ መሆኑም አግባብ እንዳልሆነ ዛሬም ይሰማኛል። ሆኖም ከተለዩን ከአንድ ዓመት በኋላም ቃላቸውን ለመጠበቅ በየአቅጣጫው የሚከናወኑት ተግባራት ዛሬም በአካል እንጂ፤ በሌላ በምንም መንገድ እንዳልተለዩን እያረጋገጠን ነው። ለትውልዶች የሚተርፉት ሥራዎቻቸውም የበለጠ እንዲታወሱም ያደርጓቸዋል።

**የመለስን ራዕይ በመተግበር የአገራችንን ህዳሴ እናስቀጥላለን!!!**